የሽማግሌ ቀልብ ለሁለት ነገሮች ወጣት ከመሆን አይወገድም: (እነርሱም) ዱንያን በመውደድና ምኞትን በማርዘም ነው።

ከአቡ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ "የሽማግሌ ቀልብ ለሁለት ነገሮች ወጣት ከመሆን አይወገድም: (እነርሱም) ዱንያን በመውደድና ምኞትን በማርዘም ነው።" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ሽማግሌ ሰውነቱ ቢጃጅና ቢደክምም ቀልቡ ግን ሁለት ነገሮችን በመውደድ በኩል ወጣት መሆኗን ተናገሩ: የመጀመሪያው: ገንዘብን በማብዛት ዱንያን መውደድ ነው። ሁለተኛው: ረጅም ህይወትን፣ እድሜን፣ ምቾትና ምኞትን መውደድ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/66221